# «ቁስለኛው ጅብና ጋኔል ጎታቹ ደብተራ»- በአፍሪካ ቀንድ

*ከግንቖ አሊሾ*

ሻእቢያን ሳስብ የቆሰለ ጅብና በሚጎትተው የተበላ ጋኔል ጎታች ወ.ዘ.ተ... ይታየኛል:: በአንድ ምክንያት:: የሻእቢያ ባህሪ ለጤናማዎች ትንታኔ ከምንጠቀመው የማህበረሰብ ሳይንስ ያፈነገጠና በአመዛኙ ለተረት ተረት እና አፈ ታሪክ ብቻ የሚመጥን መሆኑ ስለሚገዝፍብኝ:: (ስህተት ልሆን እችላለሁ፤ እንድሆንም እመኛለሁ) የቆሰለ ጅብ ቤቱ አይገባም የሚለውና ጎታች ሆኖ ከርሞ ተጎትቶ የሚሰናበተው ደብተራ አፈ-ታሪክ የዚህ ዋነኛው ገላጭ ነው:: ላብራራ::

የቆሰለ ጅብ ቤቱ አይገባም ሲባል እንደ ግስላዋ በእልህ አይደለም:: (አንዳንዶች የሻእቢያ መወራጨት ከዚህ የመነጨ ነው እንደሚሉት የተሳሳተ ግምት) ራሱን ጨምሮ መርጦ መመገብን የማያውቅ፣ እጥረትና ረሃብንም ቢሆን የማይታገስ ሆዳምነት ዋናው የጅብነት መገለጫ በመሆኑ እንጂ:: እናም ሊበላ ብሎ ተነክሶ ወይም ተወግቶ ከቆሰለው የሰውነቱ ክፍል ይጀምርና፤ ጉበቱን፣ አንጀቱን፣ ሳንባውን፣ ጡንቻውን ወ.ዘ.ተ ተራ በተራ እየቀነጨበ በመብላት መራመጃ ጡንቻ፣ መተንፈሻ ሳንባ፣ ፈጭቶ ማከማቻ አንጀት በየደረጃው ያጣል:: የራሱን አካል እንዲህ ዘነጣጥሎ ይጨርስና ነፍሱን ተሰናብቶ ሞቱን ይተቃቀፋል:: ከመንገድም ይቀራል- የቆሰለ ጅብ::

ይህን አፈ ታሪክ በመንግስት ደረጃ ጥሩ አድርጎ የሚወክል ካለ ከኤርትራው ሻእቢያ በላይ በቀዳሚው ረድፍ ላይ የቆመ አናገኝም:: ሻእቢያ ከጅምሩ 🕮ምሴ🕮 ከወታደራዊ ግዝፈትና ከጦረኝነት የሚገኝ «ታላቅነት» ነው በሚል እምነት ተንቀሳቀሰ:: ለዚህም በግብርነት የሚያቀርባቸው መስዋእቶች ባቅራቢያው የሚገኙ ሌሎች ጎረቤቶች፣ የግብር አዳራሹም ጦርሜዳና የከተማ ሽብር ሆነ:: ለሁሌ የጭዳ ግብርነት ያሰባቸው ጎረቤቶቹ ግን ለአንዴውም የሚመቹ አልሆን ብለው ማስገበሪያ ጡንቻውን ሽነቆሩት:: እንዲህም ከጡንቻው (ወታደራዊ ክፍሉ) ጀምሮ በፖለቲካ (ሳንባው)፣ በዲፕሎማሲ(ቆዳው)ና በኢኮኖሚ(አንጀቱ) ክፍሎቹ ሁሉ እየቆሰለና እራሱን እየዘነጠለ በሞት ጎዳና እየተንደረደረ መጣ:: ያውም እንደ አያ ጅቦ ከህልፈቱ ጋር ከመላተም ውጭ ቆሞ ፍጥነቱን መቆጣጠር፣ አስቦም አቅጣጫ ቀይሮ በህይወት ለመቀጠል የሚያስችል አቅም የሌለው የትም ቀሪ መንገደኛ ሆኖ::

በዚሁ አኳኋን ቀጥሎም ከራሱ ውጭ የሚያቀርበው የተለመደ ሌላ ምስ/ግብር ቸግሮት በጎተተው ጋኔል እንደሚቀረጠፈው «ጋኔል ጎታች ደብተራ» የሆነበት ደረጃ ላይ ደረሰ:: እንደ አፈ ታሪኩ ጋኔል ጎታቹ ደብተራ ከጅምሩም ከጋኔል ሊተቃቀፍ የፈለገው፣

ገብቶበትም ሊተወው ያልተቻለው አካባቢው ባሉ ፍጡራን ላይ የበላይ ለመሆን ተመኝቶ፣ ለዚህም ከዲያብሎስ የሚገኝ አቅምን በጋኔሉ አማካይነት ተመግቦ ታላቅ ባለአቅም መሆን ግድ ሊሆንበት በመቻሉ ነው:: የመጨረሻ እጣ ፈንታውም የማይቆጣጠረውን ታላቅነት ቃኘቶ የማያስቀረውን የህልፈት ፅዋ መጎንጨት ሆነ:: እስከመጨረሻዋ የህልፈት ስንብት የገፋው ህይወትም በአካላዊ መሽመድመድና በተዘበራረቀ አስፈሪ ገፅታ የታጀበ ነበር:: እንደ አፈ ታሪኩ::

ከባድመ ዛላአንበሳ እስከ ቡርሃክባና ኪስማዮ፤ ከሃኒሽ ደሴቶች እስከ ኩርሙክ ሱዳን ባለ የጦር አውድማ፣ ከአፍሪካ ህብረት እስከ አረብ ሊግ ከተመድ እስከ አውሮፓ ህብረት ባለ የዲፕሎማሲ መድረክ፣ ከኤርትራ ቲቪ እስከ አልጀዚራ ባሉ ስቱዲዮዎች ሻእቢያና መሪዎቹ የተጎነጩት ፅዋ መድረኩ ቢለያይም ይኸው «የአይቀሬ ሞት» መልከ ብዙ ፅዋ ነው:: ዛሬም እስትንፋስ ኖሮት ሲንከላወስ በህይወት አለ ቢባልም አኗኗሩ ግን ተሽመድምዶና በአስፈሪ ገፅታ ታጅቦ የመጨረሻውን ሰዓት ብቻ የመጠበቅ ነው:: ልክ እንደ «ጋኔል ጎታቹ ደብተራ»::

መንግስታዊ አሸባሪ፣ የአሸባሪ ተላላኪዎች አዝማች እና ከዓለም የተገለለ ሆኖ ይህንኑ «የአይቀሬ ሞት ፅዋ» እየጨለጠ የእድሜ አሳጣሪ ጉዞውን ፍጥነት ጨምሯል:: ላለፈው አንድ ዓመት ተኩል በተደጋጋሚ በኢትዮጵያ ላይ እየሞከረ የከሸፈበት፣ ሰሞኑንም የሰለለ እጁን ያጣበት የከተማ ሽብር መምከንም የዚህ አንድ ገፅታ ነው:: እንደ ጋኔል ጎታቹ ደብተራ መሽመድመዱ፣ እንደ ቁስለኛው አያ ጅቦም እራሱን እየቀረጠፈ ለአይቀሬው ህልፈት መቃረቡም መገለጫ ውጤቱ ነው::

የአሜሪካዋ ምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር 🕮የማታ ማታ ሻእቢያ የአፍሪካን ቀንድ ለማተራመስ ያለውን አቅም ልክ ያየዋል🕮» በማለት ከሰሞኑ የተናገሩት አባባል ምንዛሬም ለእኔ አንድ ብቻ ነው:: የቆሰለው ጅብ እንደወጣ መቅረት፣ የጋኔል ጎታቹ ደብተራም በጎተተው ተጎትቶ ኦሮማይ ብሎ የመሰናበት አፈ ታሪካዊ ፍፃሜን በሻእቢያ ህልፈት ተመስሎ በአፍሪካ ቀንድ መንግስታዊ ፍቺ አግኝቶ እናየዋለን የሚል:: በእርግጥም ጀምሯልና እናየዋለን፤ ይሆናልምና እናየዋለን::